# የ ADA እና የአካል ጉዳተኝነት መብቶች በልጆች ደህንነት ላይ የሚያሳድሩትን ተፅእኖ መረዳት



## ትርጓሜዎች

**ADA:** Americans with Disabilities Act (የአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ)

**ተጓደኝ ወይም አብሮ ሃጅ፡-** ከርዕስ II እና ክፍል 504 ጋር ስለሚገናኝ። የልጅ ደህንነት አገልግሎቶችን የሚፈልግ ወይም የሚቀበል ማንኛውም የቤተሰብ አባል፣ ጓደኛ ወይም ተባባሪ ሊያካትት ይችላል።

**DCYF:** Department of Children, Youth, and Families (የልጆች፣ ወጣቶች እና ቤተሰቦች መምሪያ)

**የአካል ጉዳት፡-** ሁለቱም ADA እና ክፍል 504 የአካል ጉዳትን እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡- "አንድ ወይም ብዙ ዋና-ዋና የህይወት እንቅስቃሴዎችን የሚገድብ የአካል ወይም የአእምሮ እክል" እንድሆነ ይገልጻሉ። ዋና-ዋና የህይወት ተግባራት እንደ እራስን መንከባከብ፣ የእጅ ስራዎችን ማከናወን፣ መተንፈስ፣ መናገር፣ መራመድ፣ ማንበብ፣ መማር፣ ማተኮር፣ ማየት፣ መስማት፣ መብላት፣ መተኛት ወይም ሥራ መስራትን በውስጣቸው ያካትታሉ። ዋና-ዋና የህይወት ተግባራት የሰውነትን በሽታ የመከላከል ስርዓት፣ የምግብ መፈጨት፣ አንጀት ወይም ፊኛ፣ ኒውሮሎጂካል፣ አንጎል ወይም የመራቢያ ተግባራትን ጨምሮ የሰውነት አካላት የሚደረጉ ተግባራትን ማከናወንን ያካትታሉ።

**ክፍል 504፡-** የ 1973 Rehabilitation Act (የመልሶ ማቋቋም ህግ) ክፍል 504 ግለሰቦች በአካል ጉዳተኝነት ላይ ከሚደርስ መድልዎ የሚከላከል የፌዴራል ሕግ ነው። ክፍል 504 እንደሚገልጸው፣ ማንኛውም ብቃት ያለው አካል ጉዳተኛ በማንኛውም የፌደራል የገንዘብ ድጋፍ በሚቀበል አካል አገልግሎቶች፣ ፕሮግራሞች ወይም ተግባራት ውስጥ ከመሳተፍ እንደማይገለል ወይም እንደማይከለከል ይገልጻሉ።

**ርዕስ II፡-** የ ADA ርዕስ II ብቁ የሆነ አካል ጉዳተኛ የህዝብ አካል አገልግሎቶች፣ ፕሮግራሞች ወይም ተግባራት ጥቅማጥቅሞች እንዳይሳተፍ ወይም እንዳይከለከል ወይም በዚህ አካል አድልዎ እንዳይደርስበት ይከለክላል። ርዕስ II የህፃናት ደህንነት ኤጀንሲዎችን እና የፍርድ ቤት ስርዓቶችን በውስጡ የያዘ ነው።

## ሓላፊነት

- ኤጀንሲው እና ሰራተኞቹ ከ DCYF ጋር ለተሰማሩ አካል ጉዳተኛ ወላጆች እና ልጆች ተደራሽ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል።
- ተሳታፊዎች ከነሱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ አገልግሎቶች እና ፕሮግራሞች መሻሻል አለባቸው።
- ፕሮግራሞች አካል ጉዳተኞች በድርጅቱ ፕሮግራሞች፣ አገልግሎቶች እና እንቅስቃሴዎች ላይ እንዲሳተፉ እና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለሁሉም እኩል የሆነ እድል መስጠት አለባቸው።
- ማዳላትን ወይም መድልዎ ለማስወገድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፕሮግራሞች በፖሊሲዎች፣ ልምዶች እና ሂደቶች ላይ ምክንያታዊ ማሻሻያዎችን ማቅረብ አለባቸው።
- DCYF እና ሰራተኞቹ ከአመልካቾች፣ ተሳታፊዎች፣ የህዝብ አባላት እና አካል ጉዳተኛ አጋሮች ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶች በረዳት ረዳት እና አገልግሎቶች አቅርቦት ውጤታማ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተገቢ የሆነውን እርምጃ ይወስዳሉ።

DCYF እና ሰራተኞቹ በግለሰብ አካል ጉዳተኝነት ላይ ተመስርተው ከግምቶች ነጻ የሆነ የግለሰብ ጉዳይ አገልግሎት እቅድ የማቅረብ ሃላፊነት አለባቸው። ወኪሉ ወይም ኤጀንሲው የWashington ልጆች፣ ወጣቶች እና ቤተሰቦች የ DCYFን ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች የማግኘት ሙሉ እና እኩል እድል እንዲኖራቸው የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት።

ስለ ADA መጠለያዎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን የ ADA አስተባባሪውን በ 360-480-7230 ያግኙ ወይም በኢሜል **dcyf.adaaccessibility@dcyf.wa.gov** ይላኩ።

## በ ADA ርዕስ II እና በክፍል 504 ስር ያሉ መሰረታዊ የሆኑ መርሆዎች

### ግላዊ የሆነ ሕክምና።

አካል ጉዳተኞች ከእውነታዎች እና ከተጨባጭ ማስረጃዎች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ መስተናገድ ወይም አገልግሎት ማግኘት አለባቸው። ለምሳሌ፣ በግለሰብ ግምገማ ያልተደገፈ፣ አካል ጉዳተኞች በአስተማማኝ ሁኔታ ወላጅነታቸውን ማሳደግ አይችሉም በሚለው የተሳሳተ እምነት ላይ በመመስረት ልጆችን ከአካል ጉዳተኛ ወላጅ ማስወገድ የተከለከለ ነው። የግለሰብ አያያዝ በ2021 የዋሽንግተን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ M.A.S.C ትኩረት ተሰጥቶታል።

**ለምሳሌ፡-**ስለ ደህንነት ስጋት ሲወያዩ፣ ውይይቱ በወላጆች ባህሪያት እና/ወይም ድርጊቶች ላይ ማተኮር አለበት። የአካል ጉዳተኝነት መኖር ብቻ መዘርዘር ወይም እንደ የደህንነት ስጋት መታየት የለበትም።

## በ ADA ርዕስ II እና በክፍል 504 ስር ያሉ መሰረታዊ የሆኑ መርሆዎች(በመቀጠል)

### ሙሉ እና እኩል እድል።

የአካል ጉዳተኞች የሆኑ ግለሰቦች የአካል ጉዳተኛ ካልሆኑ ግለሰቦች ከተሰጡ አገልግሎቶች ጋር ተመሳሳይ በሆነ የህፃናት ደህንነት ፕሮግራሞች፣ አገልግሎቶች እና ተግባራት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ወይም እንዲሳተፉ ተመሳሳይ እድሎች ሊሰጣቸው ይገባል። ሙሉ እና እኩል እድል በመስጠት ውስጥ፣ የህጻናት ደኅንነት ኤጀንሲ ምክንያታዊ ማሻሻያዎችን ማድረግ እና ውጤታማ ግንኙነትን ማረጋገጥ አለበት።

### a. አሳማኝ ምክኛት ያለው ማሻሽያ

ምክንያታዊ ማሻሻያ ማቅረብ DCYF የተሻሻሉ፣ ተጨማሪ ወይም ተጨማሪ እርዳታዎችን፣ ጥቅማ ጥቅሞችን እና አገልግሎቶችን ለሌሎች ወላጆች ተመሳሳይ ውጤት ለማግኘት ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ለማግኘት እኩል እድልን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከተሰጡት አገልግሎቶች የተለየ አገልግሎት እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል። የ2021 የWashington M.A.S.C ውሳኔ የአእምሮ/የእድገት እክል ላለባቸው ወላጆች ወይም ሌሎች ተመሳሳይ የነርቭ ሕመም ያለባቸው ወላጆች ምክንያታዊ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አጉልቶ አሳይቷል።

**ምሳሌ 1፡-** የወላጅነት ክፍሎች ከተሰጡ እና intellectual disability (የአእምሮ እክል) ያለበት ወላጅ ለመድገም እና ለመለማመድ የተለየ የማስተማሪያ ዘዴ ወይም ተጨማሪ የማስተማሪያ ጊዜ የሚያስፈልገው ከሆነ፣ ኤጀንሲው በኤዲኤ መሰረት ወላጅ እንደ ምክንያታዊ ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸውን የተራዘመ ጊዜ እና/ወይም የማስተማር ዘዴ ለወላጅ መስጠት አለበት።

**ምሳሌ 2፡-** እንደ አሰቃቂ የአንጎል ጉዳት ወይም ሌሎች የነርቭ ሁኔታዎች የአእምሮ/የእድገት እክል ያለበት ወላጅ፣ አንድን ግለሰብ ለማቀድ፣ ለመከታተል እና ግባቸውን ለማስፈጸም የሚረዱ የግንዛቤ ሂደቶች ወይም የአእምሮ ችሎታዎች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ጉድለቶች ሊኖሩት ይችላል። እነዚህ ችሎታዎች ወይም ሂደቶች ብዙውን ጊዜ እንደ አስፈፃሚ ተግባራት ተብለው ይጠራሉ እና እንደ ትኩረት ቁጥጥር፣ የስራ ትውስታ፣ መከልከል እና ችግር መፍታት ያሉ ነገሮችን በውስጣቸው ያካትታሉ። አንዳንድ የአስፈፃሚ ተግባራት ጉድለት ያለባቸው ሰዎች በስብሰባ እና በችሎት ጊዜ ግንዛቤን ለማግኘት ማስታወሻ ሰጭ ወይም ቅጽበታዊ መግለጫ ፅሁፍ እንዲሰጣቸው ሊፈልጉ ይችላሉ። የእንደዚህ አይነት አገልግሎት አቅርቦት እንደ ምክንያታዊ ማሻሻያ እና በ ADA መሰረት ውጤታማ ግንኙነትን እንደመስጠት ይቆጠራል።

### b. ውጤታማ ተግባቦት

የእውቀት (ኮግኒቲቭ) እክል ያለባቸው ወላጆች እየተሰጡ ያሉ አገልግሎቶችን መረዳታቸውን ለማረጋገጥ DCYF በ ADA ስር ውጤታማ የሆነ የግንኙነት ዘዴን መስጠት አለበት።

የእርዳታ እና አገልግሎቶች አቅርቦትን ጨምሮ — ተገቢ እርምጃዎች ፣ እንደ የምልክት ቋንቋ ተርጓሚዎች፣ ማስታወሻ ሰሪዎች፣ ግልጽ ቋንቋ መጠቀም እና ሌሎችም ተግባቦት እና ሂደት ችግር ያለባቸው ግለሰቦች የተነገረውን ወይም የተፃፈውን እንዲረዱ እና አካል ጉዳተኛ እንደሌላቸው ግለሰቦች በብቃት መነጋገር እንደሚችሉ ለማረጋገጥ — መወሰድ አለባቸው። የሕፃናት ደኅንነት ኤጀንሲዎች በግለሰብ ደረጃ ለሚጠየቀው እርዳታ ወይም አገልግሎት ቅድሚያ መስጠት አለባቸው። አንዳንድ ግለሰቦች የሚነገረውን ለመረዳት እንዲረዳቸው ምን አይነት እርዳታዎች ወይም አገልግሎቶች እንደሚሰጡ ወይም ማግኘት እንደሚችሉ ላያውቁ ይችላሉ። ውጤታማ ግንኙነትን ለማረጋገጥ የትኛውን እርዳታ ወይም አገልግሎት ማግኘት እንዳለብዎ ምንም አይነት ጥያቄዎች ከመጡላችሁ የDCYFን ADA አስተባባሪን ያነጋግሩ።

የእርዳታ እና የአገልግሎቶች ምሳሌዎች ከሌሎቹም መካከል ብቁ ተርጓሚዎች፣ ማስታወሻ ሰጫዎች፣ የእውነተኛ ጊዜ መግለጫ ፅሁፍ፣ ተደራሽ ኤሌክትሮኒክስ እና የመረጃ ቴክኖሎጂ፣ የፅሁፍ እቃዎች፣ የታገዘ የመስሚያ መሳሪያዎች ወይም ስርዓቶች፣ የድምጽ ቅጂዎች፣ የብሬይል እቃዎች፣ ትላልቅ የህትመት እቃዎች፣ ወዘተን በውስጡ ያካትታል።

እንደ መቼቱ፣ በተሳተፉት ሰዎች ብዛት እና በውይይት ርዕስ ላይ በመመስረት ውጤታማ የግንኙነት አቅርቦት የተለያየ ሊሆን ይችላል። የእርዳታው ዓይነት ወይም አገልግሎት አካል ጉዳተኛው በሚጠቀምበት የግንኙነት ዘዴ፣ እንደ ተግባቦት ተፈጥሮ፣ ርዝማኔ እና ውስብስብነት እንዲሁም ግንኙነቱ እየተካሄደ ባለበት አውድ ይለያያል።

**ምሳሌ 1፡-** መስማት የተሳነውን ወላጅ ለሚያካትቱ የጉዳይ ስብሰባዎች በአካል የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚዎችን ማቅረብ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። እንደ የቀጠሮ ቀን ወይም አድራሻ ያሉ ቀላል መልእክትዎች ፣ በእጅ የተጻፈ ማስታወሻ ወይም ጽሑፍ በቂ ሊሆን ይችላል።

*ያስታውሱ፡- ማስታወሻዎችን በመጻፍ መግባባት በጣም ቀላል ለሆኑ ንግግሮች ሊያገለግል ይችላል። የምልክት ቋንቋ በራሱ የተለየ ቋንቋ ነው፣ እንጂ እንግሊዘኛ አይደለም፣ ስለዚህ የምልክት ቋንቋ የሚናገሩ ግለሰቦች የጽሁፍ እንግሊዝኛን የመረዳት ችሎታቸው ሊለያይ ይችላል።*

**ምሳሌ 2፡-** የማስታወሻ አቅራቢ አቅርቦት በጉዳይ ሠራተኛ እና በወላጅ መካከል ለሚደረጉ ስብሰባዎች በቂ ሊሆን ይችላል፣ነገር ግን እንደ የቤተሰብ ቡድን ውሳኔ ስብሰባዎች፣የጋራ እቅድ ስብሰባዎች፣ወዘተ ያሉ ውስብስብ ስብሰባዎች የእውነተኛ ጊዜ መግለጫ ፅሁፍ ሊፈልጉ ይችላሉ።

ውጤታማ ግንኙነትን ለማረጋገጥ የአካል ጉዳተኛ ግለሰብን የሚመለከት ጉዳይ እንዳለዎት ካመኑበት፣ እባክዎን የ DCYF'ን የ ADA አስተባባሪ በ 360-480-7230 ወይም በኢሜል በ **dcyf.adaaccessibility@dcyf.wa.gov**ያግኙ።

---

*DCYF አያዳላም እና ፕሮግራሞቹን እና አገልግሎቶቹን ለሁሉም ሰው ዘር፣ ቀለም፣ ጾታ፣ ሃይማኖት፣ እምነት፣ እምነት፣ የትዳር ሁኔታ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ የዜግነት ወይም የስደተኝነት ሁኔታ፣ ዕድሜ፣ ጾታዊ ዝንባሌ ወይም የፆታ ማንነት፣ የአርበኛ ወይም የውትድርና ሁኔታ፣ የምታጠባ እናት ሁኔታ እንዲሁም ምንም አይነት የአካል፣ የስሜት ህዋሳት ወይም የአዕምሮ ስንኩልነት መኖር ወይም ውሻ የመመሪያ ወይም አገልግሎት ሰጪ እንስሳትን ቢጠቀምም በእኩልነት አገልግሎቱን ተደራሽ ያደርጋል። የዚህን እትም ነጻ ቅጂዎች በአማራጭ ቅርጸት ወይም ቋንቋ ከፈለጉ፣ እባክዎ የ DCYF Constituent Relations (DCYF ህዝባዊ ግንኙነቶችን) በ 1-800-723-4831 ያግኙ ወይም በኢሜይል* ***communications@dcyf.wa.gov*** *ያግኙ።*

DCYF PUBLICATION ADM_0024 AM (03-2024) Amharic